# ዕርቅን የሚፈልግና የሚቀበል በራሱ የሚተማመንና ደፋር ነው።

የእስከመቼ አዘጋጅ - አንዱ ዓለም ተፈራ
ጥቅምት ፳፮ ቀን ፳፻፮ ዓመተ ምህረት
November 5, 2013

በኢትዮጵያዊያን ዘንዳ፤ ይቅር ለፈጣሪ ብሎ ከተጣሉት ጋር እንዲታረቁ፤ ከልበ ሙሉዎች፣ ከባህል አክባሪዎችና ለነገ ግምት ካላቸው ሰዎች ይጠበቃል። እናም አመዛዛኝ የሆኑ፤ አክብሮት፣ ርጋታና ፍቅር ያላቸው፤ ለእርቅ ምን ጊዜም በራቸው ክፍት ነው። አጉል የሆኑት ደግሞ፤ እኔ ስህተት አልሠራም፣ እኔ ምን ጊዜም ትክክለኛ ነኝ፤ ስለሚሉና ሌላው ሁሉ ለነሱ ሰግዶ እንዲልመጠመጥ ስለሚፈልጉ፤ ለእርቅ በራቸው ዝግ ነው። አጉል የሆኑ ማለት፤ እብሪተኞች፣ ፈሪዎች፣ በራሳቸው የማይተማመኑ፣ የግልና የአሁን ሕይወታቸውና ጥቅማቸው እንጂ፤ የኅብረተሰብ ወይንም የሀገር ጉዳይ የማይዋጥላቸው ናቸው። አምባገነኖች በዚህ ክፍል ይመደባሉ። በአሁኑ ሰዓት ወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት የዕርቅ ጉዳይ በሃሳብ ደረጃ ያንሸራሽራል የሚል ወሬ ብቅ ብቅ ማለት ጀምሯል። ( በትናንቱ የጎልጉል ገፅ፤ **<u>በህወሃት ውስጥ የዕርቅ ሃሳብ መነሳቱ ተሰማ፤</u>** <u>- "የኢህአዴግ የአፈና ገመድ ነትቧል፣ ድርጅቱ ተናግቷል"</u> በሚል ርዕስ አዘጋጆች የጻፉትን ይመለከቷል ) ይኼን ሁኔታ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም አንፃር ማየቱ የግድ ነው። እናም ለማያውቅሽ ታጠኚ እንደተባለው የትም አይደርስም በማለት ሃስቤን እንደሚከተለው አቅርቤአለሁ።

በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ሀቅ ለማንኛውም ሰው ዓይን የሚያስፈጥጥ፣ ጭንቅላት የሚረብሽና እረፍት የሚነሳ ነው። ይኼን በምንም መንገድ ቢያዩት፤ የነገውን አስፈሪ መጪ ሊያስበረግገው አይችልም። አስፈሪ ነገ ከፊታችን ላይ ተገትሯል። እንግዲህ ጥያቄዎቹ፤ በአሁኑ ሰዓት ወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ይፈራል ወይ? ይኼንስ ጉዳይ እንዴት ሊያየው ይችላል? ነው። ማየቱ ብቻ ሳይሆን ምን ያደርጋል? ነው። ምን ዓይነት እርምጃ ይወስዳል? በጁ ያለውስ ምን ዓይነት አማራጭ ነው? እነዚህም ማጤኑ ይጠቅማል።

አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ሀቅ አለ። ሀገሪቱን ለገጠማት አስቸጋሪ ሁኔታ ተጠያቂው ወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ነው። ይህን ግን ግንባሩ አይቀበለውም። እንዲያውም ለዚህ ተጠያቂዎቹ “ሌሎች ናቸው”፤ “ታጋይቹ ናቸው” ነው የሚለው። “እኔ ደግ ሠሪ እነሱ በጥባጮች ናቸው” ነው የሚለው። ሲጨንቀው ደግሞ “የውጭ ሀገር ጠላቶቻችን ናቸው ይሄን የፈጠሩት” ነው የሚለው። ታዲያ መፍትሔ ፍለጋ የሚሮጠውም ይሄን ሰንቆ ነው። “እንዴት አድርጌ ነው የማጠቃቸው” ነው የሚቀናው። እናም ዕርቅ አይዋጥለትም። በተመሳሳይ መንገድ፤ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለሕዝቡ ትንሽ መፈናፈኛ የሥልጣን መንገድ አለመክፈታቸውን፤ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ከሱ ሌላ አዋቂና መፍትሔ ሠጪ የለም ብሎ ማመኑን፤ በተመሳሳይ መንገድ ደግሞ መለስ ዜናዊ የዚሁ ቅጂ መሆኑን ማጤን ይኖርብናል። ሶስቱም ገዥዎች ከራሳቸው በላይ ነፋስ ብቻ ባይ እንደነበሩ ሁላችን እናውቃለን። የሁለቱ የነጀመሪያዎቹ መጨረሻና የመለስና ግብረ አበሮቹ መጨረሻ ምን እንደሆነና እንደሚሆን አስታዋሽ አያስፈልገንም።

አንዳንዶቻችን የራሳችንን ኃላፊነት ወደ ሌላው በማሻገር፤ ህወሃት በራሱ ፈርሶ ወይንም በፈቃዱ ሥልጣን ሊያጋራ እንደሚችል ማስረጃው ሳይሆን ምኞቱ አለን። ደግ! ምኞት ብለን መቀበል አንድ ነገር ነው። ምኞት ብቻ ነው ብለን መቀበል አለብን። ከዚያ አያልፍም። በርግጥ የሕዝቡ እየደፈረ መምጣትና በተለያዩ ቦታዎች የሚነሱት ጥያቄዎች፤ ወገንተኛውን አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት መሪዎች ሊያቁነጥንጥ ይችላል። መቀመጫዎቻቸውን ከማደላደል ያለፈ ግን፤ የሚያደርጉት እንደሌለ መረዳት አለብን። ከደረስብን ግፍና በደል ተነስተን፤ ምኞታችን በዝቶ አስተሳሰባችንን እየጋረደው፤ ምኞታችንን ሀቅ እያደረግን የምንዋዥቅ ሞልተናል። ግን ታሪክ የሚያስተምረን፤ ከእባብ እንቁላል እርግብ እንዳንጠብቅ ነው። በነሱ ግምት፤ የመቀመጫቸው ድልዳል ላላ በማለቱ ነው እንጂ እነሱ በደል ሠርተው ነው የሚለው በሕልማቸው እንኳ አይዞርም። ታዲያ ለምን ብለው ያልበላቸውን ያካሉ?

በትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት መሪዎች መካከል “ዕርቅ” የሚለው ጉዳይ ለውይይት ሊነሳ ይችላል። ይኼን መቼም አይደረግም ብዬ አፌን ሞልቼ መከራከር አልችልም። በመካከላቸው አንድነት ስለሌለ፤ አንዳንዶቹ ባንድ መንገድ ሆነ በሌላ ያገኙትን ጥቅም ይዘው የተደላደለ የወደፊት ኑሮ ከፊታቸው ብልጭ ሊልባቸው ይችላል። እነዚህ ግን አቅራቢዎቹ ግለሰቦች ብቻቸውን ናቸው። ወሳኙ ደግሞ ተሰባስበው በአንድነት የሚስማሙበት ብቻ ነው። እናም ማተኮር ያለብን፤ የጠቅላላ ስብስቡ ቅኝት ምንድን ነው የሚለው ላይ ነው። የጠቅላላ ስብስቡን ቅኝት ደግሞ ከራሱ ታሪክና ከሌሎች መሰሎቹ ታሪክ የተጻፈ ስለሆነ ማወቁ አይቸግርም። ታሪክ ታስተምራለች ሲባል፤ ማገናዘቡን ለኛ ትታ ነው። ከታሪክ የማንማር ከሆን፤ አሁንም በዚያው ስንዳክር ለወጪዎቹ በሽታችንን እናተላልፍላቸዋለን። ትጥቅ መፍታት እንዳይሆን መገንዘብ አለብን። የሶሪያ ሕዝብ ከአሳድ ጋር መፋለም ሲይዝ፤ አሳድ በቃው፤ የሱ መወገድ ለድርድር አይቀርብም ብለው ነው። ለትግሬዎች ነፃ አውጭ ግንባር መሪዎች ሥልጣን ከማጣት መቃብራቸውን መቆፈር ይቀላቸዋል፤ እናም ይኼኑ እያደረጉ ነው።

እርቅ ወርዶ ሀገራችን በሰላም የወደፊቷን የምትጀምር ከሆነ፤ ከማንም በማያንስ ደረጃ ደስተኛ እሆናለሁ። በምኞት ፈርስ ግን መጋለቡን እስከዛሬ አስረጅተነዋልና የዚያ ፈረስ ጥላውም ከኔ ጋር የለም። ፈረሱ ደክሞት ሕይወቱን ጨርሶ ሞቷል። ጥላውም አብሮ ተቀብሯል።

ሀገራችን ከፊቷ የተጋረጠባት አደጋ ከባድ ነው። የተመሰቃቀለ ነው። እንዲያው አንድ ቀን ወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ተነስቶ፤ "ከዛሬ በኋላ ሁሉ ነገር ተለውጧል!" የሚልበትና የሚቀየርበት እውነታ፤ ገና መጻፊያ ቀለሙ አልተበጠበጠም።

እንዲህ ነው። ወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት መሪዎች ዕርቅ ይፈልጋሉ ብለን ስንጀምር፤ ከኛ ምኞትና እምነት ሳይሆን መነሳት ያለብን፤ ከነሱ እምነትና እውነታ ነው። መመልከቻ መነፅራችን የነሱ መሆን አለበት። ለምን ይፈልጋሉ? በነሱ እምነት፤ ጠንካራ ተቃዋሚ የለም። ሥልጣኑ ሁሉ በጃቸው ነው። ሀብቱ ሁሉ በጃቸው ነው። ጉልበቱ ሁሉ በጃቸው ነው። መንግሥታዊ መዋቅሩ ሁሉ በጃቸው ነው። የውጭ ሀገር መንግሥታት ሁሉ የሚያውቋቸው እነሱን ብቻ ነው። ብዙ የድርጅት አባላት ያሏቸው እነሱ ብቻ ናቸው። "አንዳንድ ክፍሎች ጥያቄ ቢያቀርቡ፤ በማያገባቸው ገብተው ነው፤ አለያም በጠላቶቻችን ተገፍተው ነው፤ አለያም ሥልጣን ፈላጊዎች ጓጉተው ነው፤ አለያም ትንንሾቹ ካድሬዎች አጥፍተው ነው፤ አለያም ከኛ መካከል እከሌ አጥፍቶ ነው። ስለዚህ ጠላቶቻችንን እንደመስሳቸዋለን፤ ትንንሽ ካድሬዎቻችንን ነገሩ ከጠነከረ እንገድልላቸዋለን፤ የበለጠ ከጠነከረ ደግሞ፤ ከኛ ውስጥ የበተበጠንን አውጥተን እንሰቅለዋለን። የኛን ታማኝ አባሎች በየቦታው እናስቀምጣለን፤ በተጨማሪ ደግሞ የስለላ ክፍላችንን እናጠንክራለን።" ይህ ነው የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባርና የሌሎች ከነሱ በፊት የነበሩና አሁንም የምናያቸው አምባገነኖች ግንዛቤ።

በሌላ በኩል እኛ ይኼ ሁሉ ገለባ እንደሆነ እናውቃለን። ለዚህ ነው፤ እንዲህ ስለሆነ፣ ያ በዚያ ሰለመጣ . . . እያልን የምንደራርተው። ይኼንን የተረዱ፣ የሚያውቁትና የሚቀበሉት ቢሆን ኖሮ፤ ብዙ አምባገነን መሪዎች ቀድመው የድርድር እርምጃ ይወስዱ ነበር። አላደረጉም። የኛዎቹ አምባገነኖች ከሌሎች ተለይተው አዋቂ ናቸውና ጥንቃቄ ይወስዳሉ ማለት፤ የምኞትን ቦታ የእውነት እንዲሆን ለእውነታ ማስረከብ ነው። አልፎ ተርፎም፤ ማንም ሳይጠይቀን ራሳችን ራሳችንን ትጥቅ እያስፈታን እንዳይሆን እፈራለሁ።

አሁንም አንድ ታሪክ የሚያስተምረንን ቁም ነገር እዚህ ላይ ልጥቀስ። እንደሌሎቹ አምባገነኖች ሁሉ፤ ወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት መሪዎች ሁሉ፤ ለሁሉም ጥያቄዎች ያላቸውና የሚሠጡት መልስ፤ ጥያቄውን ከነጠያቂው ግደለው! በለው! በጉልበትህ ደምስሰው ነው፤ ከሕዝቡም በኩል ይምጣ ከራሳቸው መካከል። ይልቁንስ ኢትዮጵያዊያን በአንድ ሆነን፤ አንድ አጀንዳ ብቻ ይዘን፤ ከሕዝቡ ጎን በመሠለፍ፤ እውነተኛ መፍትሔ የሚመጣበትን መንገድ አብረን እንፈልግ።

የኢትዮጵያን ነገ የሚወስነው፤ ወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት የሚያደርገው ወይንም የማያደርገው ሳይሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተገብረውና የሚጽፈው ብቻ ነው። የየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓመተ ምህረት ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብ መነሳት እንጂ፤ የንጉሠ ነገሥት ዝም ማለት አይደለም። የደርግም የመጨረሻ ታሪክ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እምቢታና የታጠቁ ኃይሎች ደርግን መደምሰስ እንጂ የደርግ ተግባር አልነበረም። አሁንም በድጋሜ፤ የነገው ታሪካችን የኢትዮጵያ ሕዝብ መነሳት እንጂ፤ ወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ተግባር አይደለም የሚጻፈው። ሲጀምርና ሲጨርስ፤ **"የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት ተነስቶ በማመፅ፤ ወገንተኛውን አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ደመሰሰ!"** ነው የሚለው።

እስከመቼ
eske.meche@yahoo.com
http://nigatu.wordpress.com/